**ስልታዊ እና ከግጭት ጋር የተያያዘ ወሲባዊ ጥቃትን የሚመለከት መረጃን መሰብሰብ እና መጠቀመን የሚመለከት ዓለም አቀፍ የሥነምግባር ደንብ**
***ሚያዚያ 5 ቀን 2014 ዓ.ም***

***መቅድም***

*ይህ አስገዳጅ ያልሆነ የሥነምግባር ደንብ ነባር የመነሻ መስፈርቶችን በማጣራት ስልታዊ እና ከግጭት ጋር የተያያዘ ወሲባዊ ጥቃት ("SCRSV")[1] ጋር በተገናኘ የተጠቂን ወይም የተጎጂን ("ተጎጂ")[2] መረጃ አስተማማኝ፣ ውጤታማ እና ስነ-ምግባርን የተከተለ የአሰባሰብ እና የአጠቃቀም መስፈርቶችን የሚያስቅምጥ ነው።እነዚህን መረጃዎች የሚሰንዱ፣ የሚመረምሩ፣ የሚዘግቡ፣ የሚያጠኑ፣ የሚከታተሉ እና በሌላ መንገድ የሚሰበስቡ ("የሚያሰባስቡ") እና እነዚህን መረጃዎች የሚጠቀሙትን ይመለከታል።*

*ደንቡ እንደ ሰብዓዊ ክብር፣ የግል ህይወት መከበር፣ ጤና፣ ደህንነት፣ ፍትህ ፣ እውነትን እና ውጤታማ ካሳን ማግኘትን የመሳሰሉ የተጎጂ መሠረታዊ ሰብዓዊ መብቶችን ጨምሮ ዓለም ዓቀፍ ህግን መሰረት ያደረገ ነው። በመሆኑም ደንቡ ተጎጂን ያማከለ አካሄድን ለመከተል በሁሉም ተዋናዮች በሁሉም አውድ ውስጥ ሊተገበሩ የሚገቡ ዓለም አቀፍ፣ የማይገረሰሱ እና አንኳር መስፈርቶችን ያንፀባርቃል። ድንቡ በግለሰቦች እና በድርጅቶች ተግባራዊ የሚደረጉ መስፈርቶችን ያካተተ ሲሆን እነዚህን መስፈርቶች በስርዓቶች፣ ፖሊሲዎች፣በአሰራር ሂደቶች፣ ውሎች እና ልምዶች ውስጥ ማካተት ይኖርባቸዋል።*

*ደንቡ የስልታዊ እና ከግጭት ጋር የተያያዘ ወሲባዊ ጥቃት መረጃን ለመሰብሰብ እና ለመጠቀም ፈቃድ ወይም ማበረታቻ አይደለም። በተለያዩ ዘርፎች ውስጥ ያሉ ጠቃሚ ሞያዊ መመሪያዎችን አያጠቃልልም ወይም አይተካም። ደንቡ ይህንን ስራ በኃላፊነት እና ተጎጂን ባማከለ መልኩ ለመስራት ብቁ ለመሆን እና ብቁ ሆኖ ለመቀጠል አቋራጭ መንገድ አይደለም።*

*ደንቡ በጋራ "እኛ" በሚል መልክ የተቀረፀው ደህንነቱ የተጠበቀ እና ይበልጥ ውጤታማ የሆነ ተጎጂችዎችን ያማከለ አሠራሮችን ለመገንባት እና ለማቆየት በጋራ ለመስራት ያለንን በፈቃደኝነት የገባነውን ቁርጠኝነት ለማጉላት ነው። "እኛ" የሚያመለክተው "ያለ እኛ፣ ስለ እኛ የሚሆን ነገር ለእኛ አይደለም" የሚለውን ጠቃሚ መርህ እና አብዛኛዎቹ መብቶቻቸውን እና ምርጫዎቻቸውን የሚያስተዋውቁ ዘጋቢዎች፣ ጦማሪዎች ፣ ጠበቆች፣ የጤና ሰራተኞች፣ አማካሪዎች ወዘተ የሆኑ ተጎጂዎች ጋር በጋራ መስራትን ያመለክታል ደንቡ ተጎጂዎችን በየደረጃው በማሳተፍ ሰፊ በሆነ የዓለም አቀፍ የምክክር ሂደት ሂደትአማካኝነት የተዘጋጀ ነው። "እኛ" ሲባል ግለሰቦችን፣ ቡድኖችን፣ ባለድርሻ አካላትን እና ድርጅቶችን በተለያዩ ዓወድ ውስጥ ያሉ መንግስታትን፣ የመንግሥታዊ ድርጅቶችን፣ ሲቪል ማህበረሰብን እና ገንዘብ ሰጪዎችን ያጠቃልላል። አብዛኛውን ጊዜ "እኛ" ብቻችንን አንሰራም ስለሆነም በዘርፎች መካከል የጋራ መስፈርቶች መኖር ግለሰቦች፣ ቡድኖች እና ድርጅቶች በኃላፊነት አብረው እንዲሰሩ ያስችሏል።*

*ይህ የሥነ-ምግባር ደንብ ተግባራዊ የሚሆነው:*

- *ከተጎጂችዎች እና ስለተጎጂዎች በቀጥታ፣ በተዘዋዋሪ፣ በአካል እና በእቀት በማንኛውም መልኩ (ዲጂታል፣ የፅሁፍ፣ የቃል፣ የኦዲዮ ቪዥዋል እና ፎቶግራፍን ጨምሮ) መረጃ ለመሰብሰብ እንዲሁም የሚከተሉ መረጃን የማጓጓዝ፣ ማስተላለፍ፣ ማከማቸት፣ መጠቀም፣ ማጋራት ወይም ማተም፣*
- *ከስልታዊ እና ከግጭት ጋር በተያያዘ ወሲባዊ ጥቃት ጋር በተገናኘ (ሰፊ እና አካታች በሆነ መልኩ በመተርጎም) ፣*
- *ማንኛዉም መሰል መረጃን የማጋራት ወይም የማተም ያካተተ አላማ ፣ ሆኖም ለድንገተኛ እንክብካቤ ወይም ተጎጂዎችን ለመርዳት መረጃ የመሰብሰብ አላማን ሳይጨምር።*

*ስለሆነምደንቡ ለምሳሌ ለሰብአዊ መብት መርማሪዎች፣ ዘጋቢዎች፣ ተቆጣጣሪዎች እና ተሚጋቾች፣ ይፋዊ መረጃዎችን የሚጠቀሙ መርማሪዎችን ጨምሮ፣ ለወንጀል መርማሪዎች፤ ሌሎች የኢሚግሬሽን እና ጥገኝነት ሰጪ ባለስልጣናት እና የሜዲኮ-ህግ ባለሙያዎችን ጨምሮ ከስልታዊ እና ከግጭት ጋር የተያያዘ ወሲባዊ ጥቃት መረጃን ለሚሰበስቡ፣ ለሚፍልጉ ወይም ለሚቀበሉ ሌሎች ባለስልጣናት እና ባለሙያዎች፤ ጋዜጠኞች፤ ተመራማሪዎች፤ ተርጓሚዎች፤ እንዲሁም ማህበረሰቡን መሰረት ያደረጉ የድጋፍ ድርጅቶች፣ ከተጎጂ ቡድኖች እና ሰብዓዊነት ሰራተኞች እንደዚህ አይነት መረጃ ለሚሰበስቡ እና ለሚያጋሩ ወይም ለሚያትሙ (ለአፋጣኝ እንክብካቤ እና ድጋፍ*

ዓላማ ከሚውል በስተቀር)ተፈጻሚ ይሆናል ። በተጨማሪም ፖሊሲ አውጪዎችን ጨምሮ በሚሾሙ፣ በሚያስተዳድሩ፣ የገንዘብ ድጋፍ በሚያደርጉ ወይም በሚደግፉ ወይም በሚያመቻቹ ሰዎች ሊተገበሩ ይገባል። ይህ ሁሉን ያቀፈ ዝርዝር አይደለም።

ደንቡ ከስልታዊ እና ከግጭት ጋር በተያያዘ ወሲባዊ ጥቃት ላይ ያለው ወቅታዊ ትኩረት የሚመነጨው ከስልታዊ እና ከግጭት ጋር የተያያዙ ወሲባዊ ጥቃት መስፈርቶችን እና አንዳንድ ለጾታዊ ጥቃት ልዩ የሆኑ ሁኔታዎችን ለምሳሌ ተጎጂዎችን የበለጠ የሚጎዱ ማህበረሰባዊ አመለካከቶች እና መገለልን ለመለየት እና ለማጥራት ከተጀመረው ተነሳሽነት ነው። ነገር ግንበደንቡ ውስጥ ያሉት አብዛኞቹ መመዘኛዎች በሌሎች ወንጀሎች እና የሰብአዊ መብት ጥሰቶች ተጎጂ የሆኑ ሰዎችን መረጃ ለመሰብሰብ እና ለመጠቀም በእኩል ተግባራዊ ይሆናሉ።

“ተጎጂ”አዋቂዎችን እና ህፃናትን (ከ18 አመት በታች ያሉ[3]) ጨምሮ በሁሉም እድሜ ያሉ ተጎጂዎችን፣ እና ሁሉንም ሥርዓተ-ጾታዎችን እና ማንነቶችን ያጠቃልላል።[4] ስልታዊ እና ከግጭት ጋር የተያያዘ ወሲባዊ ጥቃት በሴቶች እና ልጃገረዶች (ከስልታዊ ሥርዓተ ጾታ እና ሌሎች እኩልነት የሌለባቸው ሁኔታዎች ምክንያት የሚነሱ ሰፋ ያለ ቀጣይነት ያለው ሁከት ውስጥ የሚገኙ) ላይ ተመጣጣኝ ያልሆነ ተጽእኖ አለው ይህም በሕይወታቸው ውስጥ ብዙ ጎጂ ውጤቶችን የሚያስከትል እና ስራችን ላይ ተጽእኖ የሚያሳድር ነው። እንደ አካል ጉዳተኞች፣ የLGBQI+ ማህበረሰብ፣[5] ወንዶች እና ወንድ ህጻናት፣ እንዲሁም እንደዚህ ባሉ ማንነቶች ውስጥ ያሉ መደራረቦችን የመሳሰሉ የሌሎች ተጎጂዎችን ክፍል በስራችን ውስጥ ማጤን ይኖርብናል።

ደንቡ የተጎጂዎችን የግል ልዩነት ለይቶ ማወቅ እንደሚገባ እና በሚመደቡበት ቡድን ላይ ተመስርቶ ወይም በማንነታቸው አንድ ገጽታ ላይ ብቻ ተመስረቶ ግምት ከመወሰድ መቆጠብ እንደሚያስፈልግ አጽንኦት ይሰጣል።[6] ለምሳሌ፣ “ህጻናት” አንድ አይነት ቡድን አይደሉም እናም በእድሜ፣ በብስለት፣ በመቋቋም አቅም፣ በትምህርት፣ በጾታ፣ በሌሎች ማንነቶች እና በሁኔታዎች በጣም የተለያዩ ሰዎችን ያጠቃልላሉ። አቀራረባችንን ከግለሰባዊ ጥንካሬዎች፣ ፍላጎቶች እና ከተጎጂዎች እውነታዎች ጋር ማጣጣም የበለጠ ውጤታማ እና ተጎጂዎችን ያማከለ መረጃ መሰብሰብ እና መጠቀም እንድንችል ያመቻቻል።

ዝግጅት አስፈላጊ ነው። በተለይ አስፈላጊ የሆኑ ሥርዓቶች፣ ፖሊሲዎች፣ ሥነ-ሥርዓቶች፣ የአደጋ ምዘናዎች እና ዕቅዶች የሌሉን ከሆነ፣ ያልታቀደ መረጃን መሰብሰብን እና መጠቀምን ልናስወግድ ይገባል። እንዲሁም ከተጎጂዎች የሚገኙ መረጃዎች ላይ ያለንን ከመጠን በላይ የሆነ ጥገኝነት ማስተካከል ይኖርብናል። ሁላችንም የተጎጂዎች መረጃ ያስፈልገናል ብለን ከወሰንን፣ በተጎጂዎች ላይ ብዙ ፍላጎቶቻችንን እና ጫናዎችን እንፈጥራለን እንዲሁም የመጋለጥ እና እንደገና የመጎዳት ስጋቶችን እናሰፋለን። በምንችልበት ጊዜ ሁሉ፣ ተጎጂዎች ላይ ጫናን ለመቀነስ ሲባል የስልታዊ እና ከግጭት ጋር የተያያዘ ወሲባዊ ጥቃት መረጃን ከተጎጂዎች ወጪ ካሉ ምንጮች (የእውነታ ድግግሞሽ ምስክሮች እና የባለሙያዎች ሪፖርቶችን) መፈለግ አለብን።

ደንቡ በትክክል የሚተገበር ከሆነ፣ ስልታዊ እና ከግጭት ጋር የተያያዘ የወሲባዊ ጥቃት መረጃን የሚሰበስቡ እና የሚጠቀሙ ሰዎች ተጎጂዎች ላይ ያተኮረ ወይም ውጤታማ በመሆን መካከል ያለውን የተሳሳተ ምርጫ ማስወገድ እንደሚችሉ ያሳያል።

የህጉ መርሆዎች እና ግዴታዎች ሁሉም እርስ በርስ የተያያዙ፣ የሚደጋገፉ እና አስፈላጊ ናቸው። የቁጥር ቅደም ተከተሉ ቀዳሚነትን ወይም አስፈላጊነትን አያመለክትም።

| አጠቃላይ መርሆዎች | | | |
|---|---|---|---|
| ተጎጂዎችን እንደ ግለሰብ መረዳት | የተጎጂዎችን የመቆጣጠር እና ራስ ገዝ መሆንን ማክበር | ኃላፊነት ይሰማዎ ፣ ሀቀኝነት ይኑርዎ | እሴት መጨመር ወይም አለመስራት |

| የዝግጅት መርሆዎች | | |
|---|---|---|
| መዘጋጀት መሰረት ነው | ዐውዱ ማወቅ እና መረዳት | ስርዓቶችን፣ ብቃት እና ድጋፍን መገንባት |

| የትግበራ መርሆዎች | | |
|---|---|---|
| ከሌሎች ምንጮች መረጃ መሰብሰብ | ጊዜ መውሰድ፣ ቦታውን መፍጠር | በአክብሮት የተሞሉ እና ደህንነታቸው የተጠበቀ ግንኙነቶችን መፍጠር |

**አጠቃላይ መርሆዎች**

*እነዚህ በሁሉም የዝግጅት እና የትግበራ ደረጃዎች ላይ ተግባራዊ የሚሆኑ አጠቃላይ መርሆዎች ናቸው። በደንቡ በእያንዳንዱ መርህውስጥ መነበብ አለባቸው።*

## መርህ 1. ተጎጂዎችን እንደ ግለሰብ መረዳት

**1.1 ከተጎጂ ግላዊነት ጋር መላመድ:** እያንዳንዱ/እያንዳንዷ ተጎጂ የተለየ መሆኑን እናከብራለን። አቀራረባችንን እንደ እድሜያቸው፣ ጾታቸው፣ የእድገት አቅማቸው፣ የማገገም አቅማቸው፣ ከሌሎች ጋር ያላቸው ግንኙነት እና መስተጋብር፣ ማህበራዊ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ሁኔታ እና በሚደርስባቸው አድሎ በመሳሰሉ ልዩ ማንነታቸው፣ ባህሪያቶቻቸው፣ ቡድኖች እና አውድ ላይ ተመስርተን አቀራረባችንን እንቀርጻለን።[6] እኛ እንደነዚህ ያሉ አላባዎች በጊዜ እና በዐውድ እንደሚለዋወጡ እና አቀራረባችንም በዚህ መሰረት መስተካከል እንዳለበት እናውቃለን።

**1.2 አጸፋዊ ግምቶች:** ስለተጎጂዎች ወይም ስላሳለፉዋቸው ነገሮች እንዴት "መሆን ወይም ምላሽ መስጠት "እንዳለባቸው"፣ ስለተጋላጭነታቸው፣ ሰለጉዳታቸው፣ የማገገም አቅማቸው፣ ጾታቸው፣ አካል ጉዳታቸው፣ አቅማቸው፣ ብስለት፣ ታማኝነታቸው፣ ፍላጎቶቻቸው ወይም ስጋቶቻቸው ላይ ግምቶችን አንወስድም ወይም አጠቃላይ አስተያየቶች አንሰጥም።

**1.3 ተጎጂን ይጠይቁ:** ከቅድመ ዝግጅት ስራ በኋላተጎጂ ህፃናትን ጨምሮ ተጎጂዎችን ምን እንደሚፈልጉ፣ ቅድሚያ ስለሚሰጧቸው ጉዳዮች፣ ሰለ ስጋቶቻቸው፣ አደጋዎች እና ወቅታዊ ሁኔታዎች እንጠይቃለን። እነዚህን በተሰጠን ሀላፊነት እና አቅም እናከብራቸዋለን እንዲሁም እንገልጻቸዋለን።

**1.4 የተጎጂን ደህንነት ያስቀድሙ**: ከዓላማችን አስቀድመን ሁልጊዜ የተጎጂን ደህንነት፣ ጤንነት እና ክብር ቅድሚያ እንሰጣለን። ከእኛ ጋር በሚደረግ ማንኛውም ግንኙነት ምክንያት በተጎጂዎች እና በዙሪያቸው ባሉ ሰዎች ላይ የሚያደርሱትን አደጋዎች እና መዘዞች ለመረዳት እንሰራለን። እነዚህ ስጋቶች ዳግም የጥቃት ሰለባ መሆን፣ በቀል፣ መገለል፣ የአካላዊ፣ የበይነመረብ (ኦን ላይን)፣ የመረጃ እንዲሁም የግንኙነት ደህንነት ስጋቶች እና የህግ ስጋቶች ሊሆኑ ይችላሉ።

**1.5 ከፍ ያሉ ስጋቶችን መለየት:** ተጨማሪ ጉዳት የሚያስከትሉ ከፍተኛ ስጋቶች ሲኖሩ ተጨማሪ ልዩ ጥንቃቄዎችን እናደርጋለን። ማንኛውም ግለሰብ ከጊዜ ወደ ጊዜ እና በዐውድ አማካኝነት ሊለወጡ የሚችሉ ከፍ ያሉስጋቶች ሊያጋጥሙት/ሊያጋጥሟት እንደሚችሉ እንገነዘባለን። በጦርነት የተወለዱ ህጻናትን እና ከአሳዳጊ የተለዩ ህጻናትን

ጨምሮ ተጎጂ ህጻናት፣ ከLGBTQI+ ማህበረሰብ የመጡ ሰዎች፣ አካል ጉዳተኞች ወይም ማንበብ እና መጻፍ የማይችሉ ሰዎች፣ የአንድ አካባቢ የቀደመ ማህበረሰብ ተወላጆች ወይም የተገለሉ ቡድኖች፣ እና ሌሎችም ላይ ከፍ ያሉ ስጋቶች ሊፈጠሩ ይችላሉ።[6]

**1.6 *የፍትህ ተደራሽነትን መደገፍ***: እንደ ውጤታማ መፍትሄ፣ እውነታ፣ ፍትህ (እንደተጎጂው አተረጓጎም) እና ለውጥ ማምጣት የሚችሉ ካሳዎችን ማግኘት የመሳሰሉ መብቶቻቸውን የመጠቀም (ያለመጠቀም) መብታቸውን እንደግፋለን። በተጎጂ በግል ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ነገሮች፣ የመብት ጥያቄ የማራመድ ወይም የመጠየቅ ችሎታ፣ ወይም ተጠያቂነት የማምጣት ሂደቶች ውስጥ የመሳተፍ (ወይም ያለመሳተፍ) ምርጫ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ አናደርግም። ምንም እንኳን የቃለ መጠይቆች መዝገቦች ወይም ሪፖርቶች በወደፊት ሂደቶች ውስጥ ተጎጂዎችን ሊጠቅሙ ቢችሉም፣ የቀደመ የቃለ-መጠይቅ ስነ-ዘዴ እና መዝገቦች የተጎጂው ቃል ወጥነት የለውም ወይም ከልክ በላይ ተጽዕኖ የደረሰበት ነው በሚል ለመከራከር የሚፈጥረውን ከፍተኛ ስጋት እንቀንሳለን።

**1.7 *የራስን ማንነት ማክበር*:** የተጎጂን ምርጫ እና ማንነት የሚገለጽበትን መንገድ (እንደ ጾታ፣ ተውላጠ ስም፣ አካል ጉዳተኝነት እና ሌሎች ባህሪያት) እናከብራለን፣ እናንፀባርቃለን እንዲሁም ከሚያስቀይሙ፣ ስሜትን ከሚነኩ፣ ከሚያገሉ፣ ከሚያንቋሽሹ፣ አደጋ ላይ ከሚጥሉ ወይም በሌላ መልኩ ጎጂ ከሆኑ መለያዎች ወይም ባህሪያትን ከመስጠት እንቆጠባለን።

**1.8 *አካታች መሆን እና አድልዎ አለማድረግ*:** እኛ፣ ሥራችንን የሚደግፉ ሰዎችን ጨምሮ ማንኛውንም ዓይነት አድልዎ[6] አናደርግም ወይም አንታገሥም። በቅጣት፣ በመገለል፣ አቅም ወይም ችሎታ እንደሌላቸው በመገመት፣ ወይም ተጎጂ በመሆን ችላ የተባሉ ሰዎችን ለማካተት እና ምቹ ሁኔታ[7] ለመፍጠር እንጥራለን።

## *መርህ 2. የተጎጂዎችን የመቆጣጠር እና ራስ ገዝ መሆንን ማክበር*

**2.1 *ተጎጂዎችን በድንገት ከመቅረብ መቆጠብ*:** በተቻለ ጊዜ ሁሉ፣ ተጎጂ ወደ እኛ ለመድረስ እንዲወስኑወይም ከእኛ ጋር እንዲገናኙ ለማስቻል ነባር እና በጥንቃቄ በተለዩ የመድረሻ ወይም የሪፈራል መስመሮች አማካኝነት እንሰራለን ወይም አስተማማኝ መንገዶችን እንፈጥራለን። ተጎጂዎችን በራሳችን ወይም በሌላ ሰው በኩል ማግኘት (ለተጎጂው ወደ እኛ እንዲመጡ የሚመርጡበትን አስተማማኝ መንገዶች ከመፍጠር ይልቅ) የጉዳት ስጋትቶችን ይበልጥ ከፍ እንደሚያደርግ እና ተጎጂዎች እንዲተባበሩ ጫና እንደሚያሳድር እና እውነተኛ የሆነ ነጻ ምርጫን እንደሚቀንስ እንገነዘባለን።

**2.2 *የተጎጂን ምርጫዎች ማክበር***: ለሁሉም የግንኙነታችን ገፅታዎች እና ደረጃዎች ላይ መሰረታዊ በሆነ መልኩ የተጎጂን ምርጫዎች እናከብራለን። ተጎጂ ስለ ግንኙነታችን እና አላማችን፣ ስነ-ዘዴያችን፣ እና አማራጮቻቸው፣ መብቶቻቸው እና ስጋቶቻቸው፣ ሚስጥራዊነት እና መለያቻው መሰወርን፣ መረጃቸውን መጠቀምን፣ ማጋራትን ወይም ማተምን ጨምሮ ሙሉ፣ ግልጽ እና ታማኝ መረጃ ያላቸው መሆኑን እናረጋግጣለን። ተጎጂ ከእኛ ጋር ግንኙነት ለመጀመር ወይም ላለመጀመር እና በምን ምልኩ ሊሆን እንደሚችል የሚወስኑትን ውሳኔ እንዲያግዝ ሲባል ይህንን መረጃ ለመረዳት በሚቻል እና ተደራሽ በሆነ መልኩ እናቀርባለን። ተጎጂዎች ከእኛ ጋር ያለውን ማንኛውንም ግንኙነት ለአፍታ ማቆም ወይም ማቋረጥ እንደሚችሉ እና የትኛውንም የተለየ ጥያቄ ላለመመለስ መወሰን እንደሚችሉ ግልጽ እናደርጋለን። የተጎጂን ያለመሳተፍ ወይም ያለመቀጠል ውሳኔ እናከብራለን።

**2.3 *ተጎጂዎች በመረጃቸው ላይ ያላቸው ቁጥጥር***: የተጎጂዎችን የግል ህይወት መብትን እናከብራን፣ እንደግፋለን፣ ይህም በግል ታሪካቸው፣ ማንነታቸው እና ምስላቸው ላይ ያላቸውን ቁጥጥር እና ራስ ገዝነትን ያካትታል። የማንኛውንም ተጎጂዎች የግል መረጃዎችን ወይም ወሂብ (በማንኛውም መልኩ) በሚስጥር እንጠብቃለን። ያለእነሱ በግልጽ የተሰጠ ፈቃድ ያንን መረጃ አንጠቀምም ወይም አናጋራም።

**2.4 *ውሳኔ አሰጣጥን መደገፍ***: የተጎጂውን ምርጫ ለማወቅ ያለን አቅም ላይ ገደቦች ሊኖሩ በሚኖረርበት ወቅት፣ ለምሳሌ በአእምሮ ወይም በግንዛቤ እክል ወይም በግንኙነት ተግዳሮቶች ምክንያት፣ የተጎጂን ለመደገፍ እና በፍላጎታቸው እና ምርጫቸው ላይ በተመሰርቱ የውሳኔ አሰጣጥ ሂደቶች ላይ ተሳትፎ እንዲያደርጉ ለመደገፍ ምክንያታዊ በሆነ መልኩ እናስተናግዳለን።

**2.5 *ከህጻናት ጋር የውሳኔ አሰጣጥ ሂደት***: አንድ ልጅ በውሳኔ አሰጣጥ ሂደቶች ውስጥ ለመሳተፍ ያለውን መብት እናከብራለን። በህጻኑ/የህጻኗ የመሳተፍ አቅም ላይ (ዕድሜ፣ ብስለት፣ የዕድገት አቅም፣ ጉዳት እና ልምድ፣ ጾታ እና አካባቢ/ሁኔታ ከግምት በመውሰድ) የባለሙያ ግምገማ እናደርጋለን፣ እንዲሁም በተባበሩት መንግስታት የህጻናት መብቶች ኮንቬንሽን[8] ውስጥ ያሉትን አራቱን መሪ መርሆች በመከተል ህጉ ከአሳዳጊዎች ሚና አንፃር ምን እንደሚፈልግ እንረዳለን።

**2.6 *ግፊቶችን መቀነስ*:** ተጎጂዎች መረጃን እንዲያካፍሉ ጫና የሚያደርጉ ሁኔታዎችን አስቀድመን እንቀንሳለን። እነዚህ እውነተኛ ወይም ግምታዊ የስልጣን ፣ የደረጃ፣ የጾታ ወይም የእድሜ አለመመጣጠንን፣ እና የማህበራዊ ስነ-ምግባር፣ ፖለቲካዊ፣ ወይም የቤተሰብ እና የማህበረሰብ ተጽዕኖዎችን (ተጎጂዎች ለማኅበረሰባቸው ያላቸው ስጋቶች አዎንታዊ ማበረታቻዎች ሊሆኑ እንደሚችሉ በመገንዘብ ጭምር) ያካትታሉ። ይህንን ማድረጉ እነሱን እና

ማንኛውንም የፍትህ ሂደቶችን እና ውጤቶችን ሊጎዳ ስለሚችል በእኛ በኩል ተጎጂዎችን ለማስገደድ የሚፈቀድልንንማንኛውንም ህጋዊ ስልጣን አንጠቀምም።

**2.7 መረጃ ለማግኘት በማሰብ ጥቅማጥቅሞችን አለማቅረብ:** እኛ (በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ) ተጎጂ መረጃ እንዲሰጠን እንዲስማማ ለማድረግ ስንል ምንም አይነት እርዳታ፣ ድጋፍ፣ ጥበቃ ወይም ሌላ ጥቅማጥቅሞችእንደ መሰረት ወይም እነዚህን ለማቅረብ ቃል አንገባም። ነገር ግን፣ እኛን ለመተባበር ተጎጂው የሚገጥመውን ማንኛውንም የገንዘብ ወይም ሌላ ወጪ ለመሸፈን ጥረት እናደርጋለን። በተጎጂ አካባቢየሚገኙ አካላት የሚያደርጉትን እገዛ ተጎጂ ከእኛ ጋር እንዲነጋገሩ ግፊት እንዲያሳድሩ ወይም እንዲገፋፉ አናበረታታም ወይም አንደልልም።

**2.8 ተጨባጭ የሆኑ ተስፋዎችን መስጠትን ማረጋገጥ**: ተጎጂዎች መረጃዎቻቸው ጥቅም ላይ ስለሚውሉባቸው መንገዶች እና ስለሚጠበቁት ውጤቶች (ውጤቶቹ ላይ ተጽዕኖ ሊያሳድሩ የሚችሉ ማናቸውም ውጫዊ ሁኔታዎችን ጨምሮ) ሐቀኛ እና እውነተኛ መረጃን እናቀርባለን። ከተጎጂዎች ጋር ተስፋ ስለሚያደርጉት ውጤት እንወያያለን እንዲሁም ተጨባጭ በሆኑ ተስፋዎች ላይ በመመስረት ውሳኔ አንዲሰጡ እንደግፋቸዋለን።

**2.9 ውስንነቶች ላይ ግልጽ መሆን:** እኛ ማድረግ የምንችለውን እና የማንችለውን፣ ጥበቃ ልናደርግ ስለምንችለው እና ስለማንችለው እና የራሳችን ውስንነቶች እና ሙያዊ ድንበሮችን በተመለከተ ለተጎጂዎቹ ግልፅ እና ሐቀኛእንሆናለን። የተጎጂን ፍላጎት ለማሟላት አካሄዳችን ማስተካከል ካልቻልን፣ ለምን እንዳልቻልን በምክንያት እንገልፃለን። መረጃቸውን የማሳወቅ ወይም የማካፈል ግዴታ ካለብን (ለምሳሌ ወንጀሎችን ለባለስልጣናት የማሳወቅ ግዴታ፣ ለመከላከል ወይም ለህይወት አስጊ ሁኔታዎች ምላሽ ለመስጠት መግለጽ ያለብን ሲሆን)፣ እነዚህን ከተጎጂ ጋር በቅድሚያ ተወያይተን ለእኛ መረጃ ለመስጠት መቀጠል ይፈልጉ እንደሆነ ለመወሰን እንዲችሉ ጊዜ እና ቦታ እንሰጣቸዋለን።

**2.10 ፍቃዳቸውን ማንሳታቸውን ማክበር:** ተጎጂዎች በሂደቱ ውስጥ ወይም በኋላ (በማንኛውም ቃለ መጠይቅ ወቅት ጭምር) በማንኛውም ጊዜ ስምምነታቸውን የማንሳት መብታቸውን እና ማቋረጣቸውን እንዴት ማሳወቅ እንደሚችሉ እንዲያውቁ እናደርጋለን። ፈቃዱ ሲነሳ ምን ምን ማድረግ እንደምንችል እና ያለንን ውስን ቁጥጥር ግልጽ እንሆናለን። ፈቃዱ ከተነሳ እናደርጋለን ያልናቸውን እርምጃዎች እንወስዳለን።

## መርህ 3. ኃላፊነት ይሰማዎ፣ ሀቀኝነት

**3.1 የመረጃ አሰባሳቢዎች ኃላፊነት:** የተጎጂዎች ምርጫ በመረጃ አሰባሳቢዎች የሚወስዱትን ኃላፊነት የተሞላበት ውሳኔ እንደማይተካ እንረዳለን። ተጎጂ አደጋውን ለመቀበል ዝግጁ ቢሆንም/ብትሆንም እንኳን የራሳችን የብቃት፣ ደህንነት እና ሌሎች የስጋት ግምገማችን ላይ ተመስርተን ላለመቀጠል የምንወስንባቸው ሁኔታዎች ሊፈጠሩ እንደሚችሉ እንገነዘባለን። በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታዎች ወቅት፣ ከተጎጂ ጋር ግንኙነት ያለን ከሆነ፣ ስጋቶቻችንን፣ ፣ ምክንያቶቻችንን እና ማናቸውንም አማራጮችን ከእነሱ ጋር እንወያያለን።

**3.2 ሰብዓዊ ክብር እና አክብሮት**: ተጎጂዎችን በሰብዓዊ ክብር፣ በአክብሮት፣ በሰብአዊነት፣ በጨዋነት፣ በአድናቆት እንዲሁም እንደ ውሳኔ ሰጪዎች እንደግፋለን።

**3.3 መጥፎ ስም አለመስጠት:** ከኛ ውጪ የሆኑ አመለካከቶችን እና ልምዶችን፣ የራሳችን አድልዎ፣ ፍራቻ፣ ጉዳት እና ቀስቃሽ ሁኔታዎችን፤ እና ከጾታዊ ጥቃት እና ከተጎጂዎች ጋር በተያያዘ ያለንን አመለካከት፣ ቀድመን የያዝናቸው አስተሳሰቦችንእና ግምቶችን በመረዳት ረገድ የራሳችንን ውስንነቶች ፈትሸን እንጋፈጣለን። ተጎጂዎችን የሚወቅስ፣ የሚያሳፍር፣ የበለጠ የሚጎዳ፣ ጥፋተኛ የሚያደርግ፣ የሚያንቋሽሽ፣ ዝቅ የሚያደርግ፣ የሚያፌዝ ወይም ክብር የማይሰጥ ማንኛውንም መልእክት (በድምጽ አወጣጣችን፣በቃላቶቻችን፣በአካላዊ አኳሀናችን ወይም ሌሎች ድርጊቶችቻችን) አናስተላልፍም። እነሱን የተመለከተ ይህን ሊያደርግ የሚችል ምንም አይነት መረጃን አናቀርብም ወይም አናትምም።

**3.4 ትክክለኛነትን ማረጋገጥ**: ሰለተሰበሰበው መረጃ ያለን ግንዛቤ እና ያቀረብንበት መንገድ ትክክለኛ እና ከተሳሳተ አቀራረብ ወይም ግምቶች የጸዳ መሆኑን እንፈትሻለን። በተቻለ ጊዜ፣ ትክክለኝነቱን ከተጎጂ በማረጋገጥ አስፈላጊውን እርማቶች እናደርጋለን።

**3.5 ተጎጂዎችን አለመበዝበዝ**: እኛ የምናወጣጣ፣ ለግብ ማሳኪያ የምንጠቀም፣ በዝባዥ፣ ጥቃት አድራሽ፣ ተንኳሽ ወይም ተጎጂዎችን እና መረጃዎቻቸውን ለራሳችን ጥቅም የምናውል አንሆንም። ማንኛውንም አይነት ተደራቢ ጥቃት፣ ወሲባዊ ብዝበዛ ወይም በደልን ለመከላከል እና ምላሽ ለመስጠት እርምጃዎችን እንወስዳለን።

**3.6 ታማኝ መሆን**: ልንፈጽመው የማንችለውን ቃል አንገባም። ሚስጥራዊነትን መጠበቅ ጨምሮ እምነትን መጣስ ለተጎጂዎች ደህንነት እና ጤና ሰፋ ያለ ተጽእኖ እንዳለው፣ በሌሎች ላይ መተማመንን እንደሚቀንስ እና ለድጋፍ መሰናክሎችን እንደሚፈጥር እንገነዘባለን።

**3.7** ማስረጃ ሊሆኑ የሚችሉ ነገሮችን **አለማበላሸት**: ዋና ሰነዶችን፣ አካላዊ ቁሶችን ወይም ሌሎች ማስረጃዎችን ከተጎጂ ወይም ከስፍራው አንወስድም ወይም አናስወግድም፤ ይህን እንድናደርግ በተጠየቅንበት ጊዜ እንኳን፣ ሥልጣኑ ከሌለን፣ ይህን ማድረግ አስፈላጊ ነው፣ ይህንን ለማድረግ በተሻለ አቋም እና ሚና ውስጥ ያለ ሰው የሌለ እንደሆነ፣ እናም የእነዚህን ማስረጃዎች ትክክል የማስተዳደር እና የመጠበቅ አቅም ከሌለን አናደርገውም።

**3.8 ተጠያቂ መሆን**: በዚህ ህግ ውስጥ በተገለጹት ቃላቶች መሰረት ግልፅ እና ተጠያቂ እንሆናለን። ይህን ማድረግ ያልቻልን እንደሆነ በተጎጂ፣ ቤተሰብ እና ማህበረሰብ ላይ ሊደርስ የሚችለውን ጉዳት እንረዳለን። ተጎጂዎች ስለ ስራችን ለሌሎችም ጨምር ቅሬታ ለማቅረብ ያላቸውን መብት እንገነዘባለን እናም በቀጥታ ለእኛ ቅሬታ ለማቅረብ ሲፈልጉ እናዳምጣለን። ስራችንን ለማሻሻል ለአስተያየት ክፍት እንሆናለን።

## መርህ 4. እሴት መጨመር ወይም አለመስራት

**4.1 ኃላፊነት የተሞላባቸው ውሳኔዎችን ያድርጉ**: ይህንን ስራ መቼ እና እንዴት ማድረግ እንዳለበት ኃላፊነት የተሞላባቸው ውሳኔዎች ለመደገፍ በዚህ መርህ ውስጥ ያሉትን አላባዎች እንገመግማለን። የታሰበው ስራ እና ስነ-ዘዴዎቻችን አስተማማኝ፣ ውጤታማ እና ለተጎጂዎች እሴት የሚጨምሩ መሆናቸውን ለመገምገም የራሳችን ምዘና ከሌሎች በማህበረሰብ ላይ የተመሰረቱ ተዋናዮች እና የውጭ ባለሙያዎችን ጋር ከሚደረግ ምክክር ተጠቃሚ ሊሆን እንደሚችል እንገነዘባለን።

**4.2 የእኛ ሚና እና አላማ ምንድነው?**: ስለ ዓላማችን እና ሚናችንን፤ የሚናችን ውስንነቶች እና ገደቦች፤ ለምን ከተጎጂዎች መረጃ ለመሰብሰብ እንዳሰብን፤ ከማን ምን ዓይነት መረጃ እና በምን አይነት መልኩ እንደሚያስፈልገን፤ መረጃውን እንዴት ልንጠቀምበት እንዳሰብን እና ለዚያ ዓላማ ለማን ማጋራት እንደምንችል በሚመለከት ሐቀኛ እና ግልጽ እንሆናለን።

**4.3 አማራጭ ምንጮች አሉ?**: አማራጭ የስልታዊ እና ከግጭት ጋር የተያያዘ ወሲባዊ ጥቃት መረጃ ምንጮችን እንፈልጋለን በተጨማሪም ተልእኮአችን ወይም አላማችን በእርግጥ ተጎጂዎችን ቃለ መጠይቅ እንድናደርግ ወይም ከእነሱ የተወሰደን መረጃ እንድንጠቀም የሚጠይቀን መሆኑን እራሳችንን እንጠይቃለን። አማራጭ ምንጮችን ማግኘቱ በተጎጂዎች፣ በዙሪያቸው ላሉ እና በራሳችን ላይ እንዲህ ያለውን መረጃ በቀጥታ ከተጎጂዎች በመሰብሰብ ሊኖሩ የሚችሉ ስጋቶችን እንደሚያስወግድ፣ ከተጎጂዎች ላይ ጫናን እንደሚያስወግድ እና ለመሳተፍ ወይም ላለመሳተፍ ምርጫ እንዲኖራቸው ተጨማሪ ቦታ እንደሚሰጥ እንገነዘባለን።

**4.4 ያሰብናቸው ውጤቶች ተጨባጭ ሊሆኑ የሚችሉ ናቸው?**: ይህንን ስራ የምንሰራው አላማችን ባለን ሀብት፣ ጊዜ እና ክህሎቶች አማካኝነት ጉዳት ሳያስከትል በተጨባጭ መሳካት የሚችል ሲሆን ነው።

**4.5 እሴት እንጨምራለን?**: ሥራችን ወይም ተግባራችን ለተጎጂዎች ምን ተጨማሪ እሴት ወይም ጥቅም እንደሚያመጣ በሐቀኝነት እንገልጻለን። እነዚህን ከተጎጂዎቹ ጋር እንወያያለን። እንደዚህ ያለ ተጨማሪ እሴት ካለ ብቻ ስራችንን እንቀጥላለን። አንዳንድ ተጎጂዎች በእኛ ሥራ ምክንያት በቤተሰቦቻቸው፣ በማህበረሰቡ ወይም ከቡድኖቻቸው አንጻር ሊያመጣ በሚችለው ተጨማሪ እሴት እንደሚነሳሱ እንገነዘባለን።

**4.6 ከስጋቶች አንጻር የሚጨመረውን እሴት ይመዝኑ**: ማንኛውንም ተጨማሪ እሴት ከጉዳቶቹ ግንዛቤ አንጻር በጥንቃቄ እንመዝነዋለን። አደጋን የሚቀንሱ እና ለአላማ ተስማሚ የሆኑ ተለዋዋጭ ዘዴዎችን እንቀርጻለን።

**4.7 የመጥፎ ልማድ መንስኤዎችን ይመርምሩ**: በአስተማማኝ፣ በውጤታማነት እና በስነምግባር መሬመድ የማንችልበትን ከ'አስቸኳይነት'፣ 'ህዝባዊ ጥቅም'፣ በመጠን የሚገለጹ ኢላማዎች፣ 'መከላከያ' ጋር የተያያዙ ወይም ምናቸውንም ሌሎች እንደዚህ ያሉ ለመቀጠል አነሳሽ ሊሆኑ የሚችሉ ምክንያቶችን ማንኛውንም ግፊት ወይም ምክንያቶችን በትኩረት እንፈትሻለን።

**4.8 የተጋላጭነት ስጋቶችን መቀነስ**: ቀደም ሲል ስለተደረጉ ቃለመጠይቆች ወይም መረጃ ስለማጋራት ተጎጂን እንጠይቃለን፣ እናም በሂደቱ በመቀጠል ውስጥ ያሉትን አደጋዎች እና ሌሎች አማራጮችን ከተጎጂ ጋር እንወያያለን። እንደዚህ ያሉ አደጋዎች የተጎጂውን ፍትህ የማግኘት መብትን ሊጎዱ የሚችሉ ወጥነት የሌላቸው የእውነታ ዝርዝሮችንች መፍጠርን እና ለተደራቢ ጉዳት መጋለጥን፣ የግል መብት አለመከበርን እና መጥፎ ስም መስጠትን ያካትታሉ። ድጋሚ ቃለ መጠይቅ በማድረግ ፈንታ ማንኛውንም ቀደም ሲልየተሰጡመግለጫዎች ማግኘት የሚቻልባቸውን ሁኔታዎች እንደ አማራጭ ከተጎጂዎች ጋር እንነጋገራለን። አንድ ተጎጂ ቃለ መጠይቁን መቀጠል ከመረጠ/ከመረጠች፣ አስቀድመን ቃለ መጠይቅ የማድረግ አደጋን እንቀንሳለን።

**4.9 መረጃ መጋራት**: ማንኛውንም አላስፈላጊ መረጃ መሰብሰብን ወይም ለተጨማሪ ጉዳት ወይም ሌሎች ተጨማሪ በቀጥታ ከሚደረጉ ግንኙነቶች አደጋዎች መጋለጥን ለማስቀረት መረጃቸውን ከሌሎች ታማኝ ተዋናዮች ጋር እንድናካፍል ይፈልጉ እንደሆነ ከተጎጂዎች ጋር እንነጋገራለን። ማንኛውም ተጎጂ መረጃን ለማጋራት የሚወስነው ውሳኔ በመረጃ ላይ በተመሰረተ ፈቃደኝነት፣ በስጋት ትንተና በታገዘ መልኩ መሆኑን እና በአስተማማኝ፣ በብቃት እና በተጎጂዎቹ ፍላጎቶች መሰረት መተግበሩን እናረጋግጣለን።

**4.10 መረጃን መቀነስ**: እኛ ዲጂታል መረጃን ጨምሮ የተጎጂን የግል መረጃ የምንሰበስበው፣ የምናከማቸው እና የምንጠቀመው፣ ግልጽ ለሆነ ዓላማ ምክንያታዊ መሆኑ ከተረጋገጠ፣ አላማውን ለማሳካት አስፈላጊ እና ያንን አላማ ከመፈጸም አቅም ጋር ተመጣጣኝ ከሆነ እና ያንን መረጃ ለመጠበቅ ከቻልን ብቻ ነው።

## የዝግጅት መርሆዎች

*እነዚህ መርሆዎች መረጃ ከመሰብሰቡ በፊት በዝግጅት ደረጃ ላይ መተግበር እና በአፈፃፀም ደረጃዎች ወቅት መገምገም አለባቸው። ከሌሎቹ መርሆዎች ጋር በጋራ መነበብ አለባቸው::*

## መርህ 5. መዘጋጀት መሰረት ነው

**5.1 መጀመሪያ ይዘጋጁ**: መረጃ መሰብሰብ ከመጀመራችን በፊት በተለይም ከተጎጂዎች ጋር ከመገናኘታችን በፊት ጥልቅ የእቅድ እና የስጋት ግምገማ እናካሂዳለን፣ እንዲሁም አስፈላጊው እውቀት፣ አቅም፣ ቡድን፣ ፖሊሲዎች እና ሂደቶች መኖራቸውን እናረጋግጣለን። ይህ የተጎጂዎችን መብቶች ለማክበር እና ለአስተማማኝ፣ ተደራሽ፣ ሥነ ምግባራዊ እና ውጤታማ የሆኑ ውጤቶችን ለማግኘት ወሳኝ መሠረት ነው።

**5.2 ለተጎጂ ምርጫዎች ያሎትን ምቹነት ያረጋግጡ**: የተጎጂዎችን ምርጫ ለመደገፍ ከእኛ ጋር እንዴት የት እና ከማን ጋር (ጾታ፣ እድሜ፣ ዝምድና፣ ወዘተ) እንደሚገናኙ፣ በተቻለ መጠን ምቹ የሆነ ሥነ- ዘዴ እና ቡድን እናዘጋጃለን።

**5.3 ስጋቶችዎን ይገምግሙ እና ይቀንሱ**: በዐውዱ ዙሪያ ባለው ዕውቀት እና ግንዛቤ ላይ በመመስረት፣ በተጎጂዎች፣ በቤተሰባቸው እና በማህበረሰባቸው፣ በእራሳችን እና በሌሎች በሂደቱ ውስጥ በተሳተፉት ላይ ሁሉ ሊያደርሱ የሚችሉትን አደጋዎች ለይተን እንገመግማለን። እንደ ሚስጥራዊነት፣ ደህንነት፣ ጤንነት፣ ማህበራዊ ተፅእኖዎች እና መገለሎች እና ህጋዊ መብቶች ያሉ ግለሰቦች እና ሁኔታዎች ላይ የሚደርሱ አጠቃላይ እና ልዩ ስጋቶችን እንገመግማለን።[6] ይህ ሂደት እንደ ሥርዓተ ጾታ፣ ህጻናት እና መስተጋብር፣ እንዲሁም መረጃ፣ አካላዊ እና ሌሎች እንደ ደህንነት ባሉ ጉዳዮች ላይ ብቃት ባላቸው ሰዎች መደገፍ እንዳለበት እንገነዘባለን። በተጨማሪም ከተጎጂዎች ጋር መስራታችንን ከቀጠልን፣ በስጋቶቻቸው ላይ የተጎጂዎችን ሀሳብ እንጠይቃለን። አደጋዎቹን በአግባቡ መቀነስ ካልተቻለ ወደ ፊት አንቀጥልም። ይህ ግምገማ እና የመቀነሻ እርምጃዎቹ የሥራችንን ሁሉንም ገጽታዎች ይመራሉ። እንደአስፈላጊነቱ ግምገማውን እንከልሳለን።

**5.4 የርቀት ግንኙነት**: በበይነ መረብ እና በሌሎች ከተጎጂዎች ጋር የሚደረጉ የርቀት ግንኙነቶችን ልዩ ተግዳሮቶች እና ስጋቶችን መረዳት መቻላችንን እናረጋግጣለን። እነዚህም ዝግጅቶችን በተመለከተ የሚያጋጥሙ ተግዳሮቶች፤ የመገናኛ እና የውሂብ ደህንነትን፤ የተጎጂዎችን የቴክኖሎጂ ተደራሽነት፤ አገናኞችን እና አስተርጓሚዎችን ጨምሮ የተጎጂዎችን ቦታ በማጣራት የሚያግዙንን፤ የተጎጂዎችን ደህንነት እና ምቾት ደረጃዎች መከታተል፤ እንዲሁም ደህንነቱ የተጠበቀ የአደጋ ጊዜ ምላሽ ስርዓቶች ተጎጂ አካባቢ መኖሩን ማረጋገጥ ናቸው። ህጻናትን ጨምሮ ከፍ ያለ የጉዳት አደጋ ሊያጋጥማቸው ከሚችሉ ተጎጂዎች ጋር የርቀት ቃለ መጠይቅ ሊያመጣ የሚችለውን ከባድ ስጋቶች እንገነዘባለን። እንደዚህ አይነት ተግዳሮቶችን እና ስጋቶችን በአግባቡ መፍታት ካልቻልን በርቀት ግንኙነት አንቀጥልም።

**5.5 ሌላ ማን መረጃ እየሰበሰበ እንደሆነ ይወቁ**: ከተጎጂዎች ወይም ስለተጎጂዎች ሌላ ማን መረጃ እየሰበሰበ እንደሆነ እና ለምን ዓላማዎች፣ ስራችን አስፈላጊ መሆኑን እና ተጨማሪ እሴትን እንደሚጨምር እንዲሁም ለቅንጅት እና ለትብብር መሰረት እንዲሆን ለማወቅ እንሞክራለን።

**5.6 ሊገኝ ስለሚችል ድጋፍ ይወቁ**: ቢያንስ የህክምና፣ የስነ-ልቦና እና ማህበራዊ፣ የጥበቃ፣ የተጎጂዎች ተሟጋቾች እና ሌሎች የህግ አገልግሎቶችን ጨምሮ አቅርቦቶችን፣ መዳረሻዎችን እና የተጎጂ ቡድኖችን እና ተዋናዮችን (መደበኛ እና መደበኛ ያልሆኑ) ለተጎጂዎች እንለያለን። መቅረብ የሚችል ከሆነ፣ የነባር ተዋናዮች ዝርዝሮችን እና የመዳረሻዎች («ልየታን») ከግምት እናስገባለን። እነዚህ ተደራሽነታቸውን፣ ደህንነታቸው የተጠበቀ መሆኑን፣ ሚስጥራዊነትን የጠበቁ፣ ውጤታማ መሆናቸውን እና ለተለያዩ የዕድሜ፣ የአካል ጉዳተኝነት፣ የጾታ፣ ወዘተ ሁኔታ ምቹ መሆናቸውን እንገመግማለን። በሚቻልበት ጊዜ በሙሉ ተጎጂዎችን ድጋፍ ከማግኘት የሚከለክሉ መሰናክሎችን እንለያለን እንዲሁም እንቀንሳለን።

**5.7 ማስተባበር እና መተባበር**: ተጨማሪ ጉዳት እንዳይደርስ ሲባል፣ በተጎጂዎች ከመጠን በላይ ተጋላጭ መሆንን እና በስራችን አጠቃላይ ውጤቶች አማካኝነት በመብታቸው ላይ አሉታዊ ተጽእኖዎችን ለማስቀረት ባለብዙ ዘርፍ ቅንጅት እና ትብብር የሚኖረውን አስፈላጊነት እንገነዘባለን። ተገቢ ሆኖ ሲገኝ በተመሳሳይ ጉዳዮች ላይ የሚሰሩ ሌሎች፣ የሰብአዊ እርዳታ ተዋናዮችን እና ማህበረሰብን መሰረት ያደረጉ ድርጅቶችን ጨምሮ፣ በደህንነት አብሮ ለመስራት ወይም እርስ በርስ የሌላችንን ስራ የመጉዳት ስጋቶችን ለመቀነስ ሲባል ግንኙነቶችን እንፈጥራለን።

**5.8 ሳይጠበቅ ይፋ ሊሆን ስለሚችል መረጃ መዘጋጀት**: አንድ ሰው እኛ ሳንጠብቀው ወይም ስለ ጥቃቱ ለመጠየቅ ሳናስብ ስለ ወሲባዊ ጥቃት ለመግለጽ ሊመርጥ/ልትመርጥ እንደሚችል/እንደምትችል እንረዳለን። ለዚያ ሁኔታ እንዘጋጃለን።

**5.9 ክትትልን ምስቻል**: ተጎጂዎች እና የመረጃ ሰብሳቢዎች ከተገናኙ በኋላ ቀጣይ ግንኙኑነት መኖሩ ማንኛውንም ቅጣይ የደህንነት ስጋቶችን ለማጋራት፣ ስምምነትን ለማቆም ወይም ለማደስ እና ለተጎጂዎች ስለ ተደረሰበት ደረጃ እና ውጤቶች አስተያየት መስጠት ለመሳሰሉት ምክንያቶች ወሳኝ ሊሆን እንደሚችል እንረዳለን። ውጤታማ እና ደህንነቱ የተጠበቀ የመገናኛ መንገድ ለማፍጠር እንጥራለን። ይህን ማድረግ ካልቻልን ለምን እንደማንችል በቅድሚያ

ከተጎጂ ጋር እንወያያለን። ለተጎጂ ህጻናት፣ ከህጻናት ተንከባካቢ ጋር ለመገናኘትን ለማስቻል፣ በተቻለ መጠን በህጻናት ጥበቃ ባለሙያ ድጋፍ ልዩ እርምጃዎችን እንወስዳለን።

**5.10 ለቡድንዎ እና ለሥራ አጋሮችዎ ገለፃ ያድርጉ**: ቡድናችንን እና እኛን ወክለው የሚሰሩ (ማንኛቸውንም አጋሮችን ጨምሮ) በዝግጅቶቻችን እና በደህንነት፣ ስነ-ምግባራዊ እና ውጤታማ ሂደቶች ላይ ይህን ህግ እንዲያከብሩ ገለጻ እና ክትትል እናደርጋለን።

## መርህ 6. ዐውዱን ማወቅ እና መረዳት

**6.1 አውዱን ማወቅ**: ቡድናችን እና እኛን ወክለው የሚሰሩት ስራቸውን ስልታዊ እና ከግጭት ጋር የተያያዘ ወሲባዊ ጥቃት በተከሰተበትን አውድ እና በተጎጂው ዙሪያ ያለውን አካባቢ በደንብ በመረዳት ላይ የተመሰረተ መሆኑን እናረጋግጣለን። በዚህ መርህ የሚገኙ አላባዎች በተጎጂዎች፣ በቤተሰቦቻቸው እና በማህበረሰባቸው እንዲሁም በስራችን ላይ የሚያደርሱትን አዎንታዊ እና አሉታዊ፣ ቀጥተኛ እና ቀጥተኛ ያልሆነ ተጽእኖን እንለያለን፣ ይህ ግንዛቤ ለዝግጅታችን እና ለስራችን መጋቢ መሆኑንም እናረጋግጣለን።

**6.2 ባህልን መረዳት**: አስፈላጊ ባህላዊ እና ማህበራዊ ደንቦችን፣ አመለካከቶችን፣ ወጎችን፣ ስርዓቶችን እና ልማዶችን እንዲሁም ስለ ህጻናት፣ ስለ ውሳኔ አሰጣጣቸው እና ሰለአዋቂነት እድሜቸው ያሉ አመለካከቶችን እንለያለን።

**6.3 ሥርዓተ-ጾታን መረዳት**: የሥርዓተ-ጾታ ሁኔታዎችን፣ ደንቦችን፣ጥቃትን እና የእኩልነቶች አለመኖርን እንገመግማለን፣ እንዲሁም የድርብ ጥቃት ስጋቶች እንዴት በተጎጂዎች ድጋፍ እና ሌሎች መብቶች ላይ እንቅፋት እንደሚፈጥሩ ግንዛቤ እንወስዳለን።

**6.4 በስልታዊ እና ከግጭት ጋር የተያያዘ የወሲባዊ ጥቃትን እና በተጎጂዎች ላይ የሚደርስ መገለልን መረዳት**: ጾታዊ ጥቃት እና ተጎጂዎችን በተመለከተ በማህበረሰቦች ውስጥ ያሉ ጎጂ የተሳሳቱ አመለካከቶችን፣ ግምቶችን፣ ፀባይ እና ባህሪን (‹መገለል› በመባል የሚታወቁትን) ለይተን፣ የስጋት ምዘና ሰርተን እንቀንሳለን።

**6.5 የማህበረሰብ ተለዋዋጭ ሁኔታዎችን መለየት**: እንደ ሃይል መዋቅር፣ የሃብት ፉክክር፣ ፍትህን ፖለቲካዊ ማድረግ፣ የአገናኞች የሚያነሳሱ ነገሮች፣ ጠባቂዎች (ተጎጂዎችን ማግኘትን ሊወስኑ ወይም ተጽዕኖ ሊያሳድሩ የሚችሉ)፣ ተጎጂዎችን ወይም ቤተሰቦቻቸውን ዝም የሚያሰኙ፣ የሚጫኑ ወይም የሚጎዱ እንደ ሀይል ሰጪ ተጽዕኖዎች እና ገፋፊዎች ያሉ በተጎጂዎች ዙሪያ ያሉ የቡድን ተለዋዋጭ ሁኔታዎችን እንመረምራለን።.

**6.6 የግል፣ የተቀላቀሉ እና የጋራ ጉዳቶችን ለይቶ ማወቅ**: በግለሰቦች እና እንደ ቤተሰቦች እና ማህበረሰቦች ባሉ ቡድኖች ላይ በስልታዊ እና ከግጭት ጋር የተያያዘ ወሲባዊ ጥቃት የሚደርሱ ጉዳቶችን በተመለከተ ተያያዥ የሆኑ የተለያዩ ጉዳቶችን እንመረምራለን።[6]

**6.7 ህጎችን እና ልምዶችን ማወቅ**: አግባብነት ካላቸው መደበኛ እና መደበኛ ያልሆኑ ህጎች እና ተግባራት (ሲወርዱ ሲዋረዱ የመጡ ስርዓቶችን ጨምሮ) ጋር እራሳችንን እናስተዋውቃለን። እንደዚህ ያሉ ህጎች እና ልማዶች ለምሳሌ ለተጎጂዎች ህጋዊ መንገድ ሊፈጥሩ፣ አድልዎ ሊያደርጉ ወይም መድልዎን ሊያስቀጥሉ፣ በደረሰው ነገር ተጎጂን ወንጀለኛ ሊያደርጉ፣ ተጎጂዎችን እንደ ወንጀል ሰለባ ላይወስዱ ወይም ለባለስልጣናት ስለ ወንጀል መረጃ እንድንሰጥ በህግ ሊያስገድዱ ይችላሉ። ተጎጂዎች ልምዳቸውን ማካፈል ወይም አለማካፈላቸውን እና እንዴት መቀጠል እንዳለባቸው እንዲያስቡ ልምዳቸውን ከማካፈላቸው በፊት በእነዚህ ጉዳዮች ላይ እንወያያለን።

**6.8 ተገቢ ግንኙነቶችን እና ልውውጦችን መረዳት**: ጾታን፣ እድሜን፣ አካል ጉዳተኝነትን፣ ማህበራዊ፣ ባህላዊ እና አውድን ባማከለ እና ባከበረ መልኩ በዐውዱ ውስጥ ሁሉም አይነት ግንኙነቶቻችን እና መስተጋብሮቻችን ያላቸውን ጠቀሜታ እና ተፅእኖ ለመረዳት እንሰራለን። የተጎጂዎችን ማንነት የሚያንፀባርቁ እና ጎጂ ያልሆኑ ማህበራዊ ደንቦችን እና ልምዶችን የሚያከብሩ አካታች እና ጎጂ ያልሆኑ የመገናኛ ዘዴዎችን ለይተን እንጠቀማለን። እንዲሁም ባህላዊ እና ሌሎች የግንኙነት ዘርፎችን፤ አክብሮትን፣ አዋራጅ ቃላትን፣ የተለመዱ አባባሎች እና አገላለጾችን፣ እና ከስልታዊ እና ከግጭት ጋር የተያያዘ ወሲባዊ ጥቃት ጋር ወይም ከጥቃቱ ከተረፉት ጋር የተያያዙ የቋንቋ ክፍተቶችን ጭምር ለመረዳት እንጥራለን።

**6.9 አሉታዊ ውጤቶችን መቀነስ**: በማህበረሰቡ ውስጥ የምንሰራው ስራ የሚያስከትለውን ስጋት ለይተን ማንኛውንም አሉታዊ መዘዝ እንቀንሳለን።

**6.10 ማህበረሰብ ተኮር ዘላቂ ድጋፍ**: ለተጎጂዎች የሚደረገው ድጋፍን ቀጣይነት፣ ታማኝ ግንኙነቶችን ለመገንባት፣ ተጎጂዎችን ለማነቃቃት እና በማህበረሰቡ ውስጥ ተጎጂዎች ላይ ያሉ አሉታዊ አመለካከቶች ለመቅረፍ የታመኑ የማህበረሰብ አቀፍ ቡድኖችን እና የድጋፍ ሥርዓቶችን ጠቃሚ ሚና እንገነዘባለን። እንደነዚህ ያሉ ቡድኖች የተጎጂዎች ኔትወርኮችን፣ የሴቶች ድርጅቶችን፣ LGBTQI+ ድርጅቶችን፣ የህጻናት ድርጅቶችን፣ እና የአካል ጉዳተኞች ድርጅቶችን ሊያካትቱ ይችላሉ። ተገቢ ሆኖ ሲገኝ ከእንደዚህ አይነት ቡድኖች ጋር ለመስራት እንጥራለን።

## መርህ 7. ስርዓቶችን፣ ብቃትን እና ድጋፍን መገንባት

**7.1 ተቋማዊ ሀላፊነቶች እና ድጋፍ**: ይህንን ስራ ብቻችንን እንደማንሰራ እንገነዘባለን። አብዛኞቻችን የምንሰራው በድርጅቶች ውስጥ ወይም ለድርጅቶች ነው። በድርጅቶች ውስጥ ይህንን ህግ በአመራር እና በቁርጠኝነት፣ በፖሊሲዎች፣ በሂደቶች እና በሃብት ከአማካሪዎች ጋር በተያያዘም ጭምር እንተገብራለን።

**7.2 እንደ ገለልተኛ አካል በኃላፊነት መስራት፡** በተናጥል በምንሠራበት ጊዜ እና በተቋማዊ ድጋፍ ላይ መመርኮዝ ሳንችል፣ ሥራችን በነባር አስተማማኝ የድጋፍ ሥርዓቶች እና መሠረተ ልማቶች፣ እንዲሁም በዚህ ደንብ መሠረት የገባነውን ቃል ኪዳናችንን በሚጋሩ ግለሰቦች እና አጋሮች የተደገፈ መሆኑን ለማረጋገጥ እንሞክራለን።

**7. 3 ትክክለኛውን ቡድን እና አጋሮችን መምረጥ**: ቡድን እንገነባለን (አስተርጓሚዎችን፣ አገናኞች፣ አስጎብኚዎችን፣ አመቻቾችን ጨምሮ) እንዲሁም ሌሎች ለዚህ ደንብ የገባነውን ቃልኪዳን የሚጋሩንን አጋሮች እንመርጣለን። በተጨማሪም የእነዚህን ምርጫዎች ብዝሃነት፣ ውክልና፣ ሚስጥራዊነት፣ ደህንነት እና የተለዋዋጭነት አንድምታዎችን እንመለከታለን።

**7.4 ትክክለኛ ብቃቶችን መገንባት**: ይህንን ስራ የምንሰራው በቡድናችን ውስጥ አስፈላጊው እውቀት፣ ችሎታ እና አስተሳሰብ ሲኖረን ብቻ ነው። እነዚያ ብቃቶች፡ የወሲባዊ ጥቃት እና የመገለል ግንዛቤ፤ ጾታን፣ ብዝሃነትን እና ዐውድን መረዳት፤ ከተለያዩ ጾታዎች፣ አካል ጉዳቶች እና ዕድሜዎች ጋር አብሮ መስራት፤ በግልጽ የተሰጠ ስምምነት እና መሰረታዊ የማስተላለፍ ክህሎት፤ አደጋን መለየት፤ ከህጻናት ጋር እና በርቀት የሚደረጉ ቃለመጠይቆች ጋር የተገናኙትን ጨምሮ ደህንነቱ የተጠበቀ ግንኙነት እና ቃለ መጠይቅ የማድረግ ችሎታዎች፤ የስሜት መቃወስ ግንዛቤን፤ እና የመረጃ ጥበቃ እና አቀማመጥን ያካትታሉ። ይህንን ስራ ደህንነቱ የተጠበቀ እና ለታለመለት አላማ ውጤታማ እንዲሆን የሚያደርጉትን ክህሎቶች እና እውቀቶች ወቅታዊነት እንጠብቃለን።

**7.5 ያለብንን የአቅም ውስንነቶች ማወቅ**: እያንዳንዱ ሰው በተሞክሮው፣ በዕውቀቱ እና በአመለካከቱ እንዲሁም በሚጫወተው ሚና ወይም ኃላፊነት ገደብ እንዳለው እንገነዘባለን። እውቀታችንን፣ ችሎታችንን እና ግንዛቤያችን በተመለከተ ስላሉን ወሰኖች በሀቀኝነት እናሰላስላለን እንዲሁም በእነዚህ ወሰኖች ውስጥ እንቆያለን።። ከአቅማችን በላይ በሆኑት ላይ የስሜት መቃወስ፣ የደህንነት እና የህጻናት ከመሳሰሉ ሌሎች ባለሙያዎች ጋር እንመካከራለን እንዲሁም አብረን እንሰራለን።

**7.6 ከተጎጂ ህጻናት ጋር ቃለ መጠይቅ ማድረግ**: ከህጻናት ጋር የሚደረጉ ደህንነታቸው ያልተጠበቁ እና ውጤታማ ያልሆኑ ቃለመጠይቆች ከሚያመጧቸው ስጋቶች አንፃር፣ ለተጎጂ ህጻናትን ቃለ መጠይቅ የምናደርገው ከህጻናት ጋር ለመስራት የሚታይ ብቃት፣ ችሎታ እና ልምድ ካለን እና ከተጠቀምንበት ብቻ (ከእድሜያቸው፣ የሚያድግ አቅም፣ ችሎታ፣ ጾታ እና ፍላጎት ጋር የተጣጣመ) ነው። በቡድናችን ውስጥ እነዚህ ብቃቶች ከሌሉን፣ ለመሳተፍ የሚፈልጉ ህጻናት ደህንነታቸው ተጠብቆ ውጤታማ በሆነ መልኩ መሳተፍ እንዲችሉ ብቃቱ እንዲኖረን እንሞክራለን ወይም ሌሎች ብቃቱ ያላቸውን ለመለየት እንሞክራለን።

**7.7 ተገቢውን ድጋፍ ማረጋገጥ**: እኛ መስራት የምንችለው ለተጎጂ ፍላጎቶች ምላሽ መስጠት የሚችል አግባብነት ያለው፣ ተደራሽ የሆነ ድጋፍ ሲኖር ብቻ ነው። ይህ የህክምና፣ የስነ-ልቦና እና ማህበራዊ፣ የጥበቃ እና የህግ ድጋፍን ያካትታል። እነዚህን አማራጮች ከተጎጂ ጋር ተነጋግረን ምርጫቸው ከሆነ ደህንነቱ በተጠበቀ መልኩ እንዲተላለፉ እንረዳለን። እነዚህ ፍላጎቶች አጣዳፊ ከሆኑ ከሥራችን በፊት ተደራሽነትን እና ሪፈራሎችን እናስቀድማለን። ከተጎጂዎች ጋር ከመገናኘታችን በፊት፣ በምንገናኝበት ወቅት እና በኋላ ለድንገተኛ ፍላጎቶች ድጋፍ ተደራሽነት ግልፅ እቅድ እናዘጋጃለን።

**7.8 የሚስጥራዊነት ጥበቃዎችን መገንባት**: የማንኛውንም ዲጂታል ግንኙነቶች፣ የውሂብ አስተዳደር እና ማከማቻ ደህንነት ለማረጋገጥ ልዩ ጥንቃቄ ማድረግን ጨምሮ የተጎጂን መረጃ፣ የግል ህይወት መብት እና ደህንነት ለመጠበቅ የሚስጥራዊነት ፕሮቶኮሎችን እና እርምጃዎችን እናስቀምጣለን።

**7.9 ቀጣይነት እና ወጥነት**: የመተማመን እና የምቾትት መጠንን ለማስጠበቅ እና በሰራተኞች ለውጥ ሊመጡ የሚችሉ አደጋዎችን ለመቀነስ ተመሳሳይ ሰው ከተጎጂዎች ጋር መገናኘቱን እናረጋግጣለን ። ተጎጂዎች ሰራተኞችን ወይም የሚያገኛቸውን ሰው ለመለወጥ የሚያነሱዋቸውን ማንኛውንም ጥያቄ እንነጋገራለን፣ ጥያቄያቸውንም እናከብራለን።

**7.10 ከሌሎች በኩል የሚመጣ የስሜት መቃወስን ስጋትን መቆጣጠር**: ስራው በራሳችን፣ በቡድናችን እና በሌሎች ተጽእኖ በደረሰባቸው ላይ ሊያደርስ የሚችለውን ጉዳት ለመቀነስ የሚያስችሉ እርምጃዎች መቀመጣቸውን እናረጋግጣለን። በስሜት መቃወስ፣ **ከሌሎች በኩል የሚመጣ** የስሜት መቃወስ፣ የርህራሄ ድካም እና መዛል ምልክቶች እና መገለጫዎች ላይ መሰረታዊ ስልጠናዎች መኖራቸውን እና ተቋማዊ እና የቡድን ድጋፍ ፕሮቶኮሎችን እና ደህንነቱ የተጠበቀ የስራ ዘዴዎች መኖርን እናረጋግጣለን። በርቀት መስራትን ጨምሮ ሰዎች ከቡድን ወይም ከቢሮ አካባቢ ውጭ ሲሰሩም እነዚህን አደጋዎች ለመቆጣጠር የሚያስችሉ እርምጃዎችን እናካትታለን።

**የትግበራ መርሆዎች**

*እነዚህ መርሆች መረጃ መሰብሰብ ስንጀምር መተግበር አለባቸው። ሆኖም ግን ከሁሉምሌሎች መርሆች ጋር በጋራ መነበብ ይኖርባቸዋል።*

## መርህ 8. መረጃን ከሌሎች ምንጮች መሰብሰብ

**8.1 ስለተጎጂዎች ወይም ከተጎጂዎች ያልሆነ የስልታዊ እና ከግጭት ጋር የተያያዘ ወሲባዊ ጥቃት መረጃን ይፈልጉ፡** ስልታዊ እና ከግጭት ጋር የተያያዘ ወሲባዊ ጥቃትን የሚመለከትጠቃሚ መረጃ የሚገኘው ሁል ጊዜ ከተጎጂ ወይም ስለተጎጂ እንዳልሆኑ እንገነዘባለን። ስለ ስልታዊ እና ከግጭት ጋር የተያያዘ ወሲባዊ ጥቃት መረጃ ከሰፊ ምንጮች (እንደ ስታቲስቲክስ፣የባለሙያ ዘገባዎች ወይም ትንተና እና የወንጀል አድራጊ መረጃ) ለመሰብሰብ እና ለመጠቀም እንሞክራለን ምክንያቱም ይህ መረጃ ለተጎጂዎች አነስተኛ ስጋት የሚፈጥር እና በተጎጂዎች መረጃ ላይ ከመጠን በላይ መመርኮዝን ሊቀንስ ስለሚችል ነው።

**8.2 ወካይ የሆነ መረጃን መፈለግ**: ማንነታችን፣ የምንፈልገው ነገር፣ እና እንዴት እና የት እንደምንፈልግ የምናገኘው መረጃ ጎጂ አድሎአዊ እና ክፍተት ሊያመጣ እንደሚችል እንገነዘባለን። እንዲሁም ተመሳሳይ አድሎዎች እንደ ሳንሱር፣ እኩልነት አለመኖር፣ ማህበራዊ መገለል፣ የደህንነት እጦት እና ቴክኒካዊ ሁኔታዎች  የመሳሰሉ በመረጃ አቅርቦት ላይ በሚደረጉ ገደቦች እንደሚመጡ እንገነዘባለን። እነዚህን አደጋዎች ለመቀነስ እንጥራለን።

**8.3 በተዘዋዋሪ መንገድ ከተገኙ መረጃዎች የሚመነጩ መብቶችን እና አደጋዎችን መረዳት**: ምንም እንኳን መረጃው በሕዝብ በይፋ፣ በማህደር ውስጥ ወይም ከበይነ መረብ (ይፋዊ እና ይፋዊ ያልሆኑትን ጨምሮ) ምንጮች ሊወሰድ የሚችል ቢሆንም ከተጎጂ ወይም ስለተጎጂ በተዘዋዋሪ  የተገኘ መረጃን ከመሰብሰብ፣ ከመቀበል ወይም ከመጠቀም የግል ህይወት መብት፣ የህግ እና የደህንነት አንድምታዎች እንዳሉ እንገነዘባለን። ደንቡ እንደነዚህ ያሉትን መረጃዎች መሰብሰብ እና መጠቀም ላይም እንደሚሠራ እንገነዘባለን።

**8.4 የተጎጂን ፍላጎት ማረጋገጥ**: በተዘዋዋሪ የተገኘ የስልታዊ እና ከግጭት ጋር የተያያዘ ወሲባዊ ጥቃት መረጃን (የተጎጂዎችን ፎቶዎች እና ቪዲዮዎችን ጨምሮ) መረጃው የት፣ መቼ እና እንዴት እንደተገኘ፣ እንዲሁም ከተጎጂ ለምን ጥቅም ላይ እንዲውል ምን አይነት ፈቃድ እንደተሰጣቸው እና በኋላ ለመጠቀም ቀድሞ የነበረ ፍላጎት ወይም ፈቃድ  ተሰጥቶ ከነበረ እናረጋግጣለን። የተጎጂን መረጃ ለእኛ ዓላማ ጥቅም ላይ እንዲውል የተጎጂ  ፍላጎት እና ፈቃድ መኖሩን ማረጋገጥ ካልቻልን እና ተያይዘው የሚመጡ ስጋቶችን እና ጉዳቶችን መቀነስ ካልቻልን መረጃውን አንጠቀምም ወይም አናጋራም።

**8.5 በሰብአዊ አገልግሎቶች ላይ ያለ እምነትን አለማሳጣት**: ለተጎጂዎች ድጋፍ እና እንክብካቤ አቅርቦት ለመስጠት ሚስጢራዊነት እና የእምነት ያለውን አስፈላጊነት እናከብራለን እናም አንድ ተጎጂ ለማጋራት ፈቃደኛ ያልሆነውን መረጃ የድጋፍ አገልግሎት ሰጪዎች  እንዲያካፍሉ አንጠይቅም ወይም አንገፋፋም።

## መርህ 9. ጊዜ መውሰድ፣ ቦታውን መፍጠር

**9.1 ተዘጋጅ**: ከተጎጂዎች ጋር ለመስራት ሀሳብን ሳይከፋፍሉ በክፍት አእምሮ፣ ግምታዊ ሳይሆኑ ወይም ባለመፍረድ ለማዳመጥ ዝግጁ መሆን፤ ምላሾቻችንች በግንኙነቶቻችን ላይ ተጽእኖ ሳያደርጉብን፤ እንዲሁም እምነትን ለመገንባት እና ተጎጂዎች ታሪካቸውን የሚናገሩበትን መንገድ እንዲቆጣጠሩ ለመፍቀድ ዝግጁ መሆን እንደሚያስፈልገን እንገነዘባለን። በዚያ አይነት የአዕምሮ ሁኔታ ውስጥ ካልሆንን በዚያን ወቅት አንቀጥልም።

**9.2 የጊዜ ጫናን ይቀንሱ**: በፈቃደኝነት እና በመረጃ ላይ የተመሰረተ ውሳኔ አሰጣጥን ለማበረታታት የጊዜ ጫናዎችን ለማስወገድ እና ተጎጂዎች መረጃቸውን በሚፈልጉት መንገድ እና ፍጥነት እንዲያካፍሉ ለማድረግ እንጥራለን። ልክ በጥድፊያ እንደሚደረግ ንግግር፣ ረጅም ንግግርም የጫና አይነት እንደሆነ እና ለተጎጂዎች በተለይም ለህፃናት ምቾት እጦት መንስኤ ሊሆን እንደሚችል እንገነዘባለን። መብታቸውን ለመጠቀም ተጎጂ  ሊረዷቸው የሚገቡ  ቋሚ የጊዜ ገደቦች ካሉ፣ እነዚህን ከተጎጂ ጋር እንነጋገራለን።

**9.3 ድጋፍ ሰጪ አካባቢ ይፍጠሩ**: ተደራሽ የሆነ እና ጾታ፣ እድሜ፣ አካል ጉዳተኝነት፣ ማህበራዊ፣ ባህላዊ እና አውድን ያማከለ ለአካላዊ እና ለማንኛውም በርቀት ለሚደረግ ግንኙነት ደጋፊ የሆነ፣ አካላዊ እና ስነልቦናዊ ደህንነቱ የተጠበቀ አካባቢ እንፈጥራለን። ይህ እምነትን ለመገንባት፣ ልምዶችን ለመተረክ እና ተጎጂዎችውሳኔ እንዲሰጡ ለማድረግ መሰረታዊ ነው።

**9.4 የግል ህይወት መከበርን እና መጠበቅን ያረጋግጡ**: ከተጎጂ ጋር በመመካከር፣ በአካልም ሆነ በርቀት ለመገናኘት ሚስጥራዊ፣ ድብቅ፣ ተደራሽ እና ደህንነቱ የተጠበቀ ቦታ እናዘጋጃለን፣ እንዲሁም የመታየት (ወደቦታው ሲደርሱ ወይም ሲወጡ ጨምሮ)፣ የመስማት ወይም የመቋረጥ ስጋትን እንቀንሳለን ። የተጎጂ **የግል ህይወት መከበር መብት ማንኛውም ከስብሰባ በፊት እና በኋላ ያሉ ሁሉንም ተግባብ እና ግንኙነቶችን ጨምሮ ሁሉንም አይነት ግንኙነተት እንደሚያካትት እናከብራለን።**

**9.5 በቃለ መጠይቁ ላይ ማን ይሳተፋል**: በቃለ መጠይቅ ወቅት የሚገኙ ሰዎች ቁጥርን ለመቀነስ እንጥራለን። ከተጎጂዎች ጋር ማን እንዲገኝ እንደሚፈልጉ እና ከቡድናችን ሊሳተፍ የሚችለውን (እንደ ሚናቸው፣ ጾታቸው፣ እድሜ እና ግንኙነትቶቻቸው ያሉ መረጃዎችን በማቅረብ) እንወያያለን። ድጋፍ ሰጪ ሰው፣ አሳዳጊ ወይም የህግ ተወካይ መገኘትን ጨምሮ፣ የተጎጂዎችን ምርጫዎች ማክበር ካልቻልን፣ ለዚህ ምክንያቱን ከነርሱ ጋር ተነጋግረን ለማቋረጥ ከወሰኑ ምርጫቸውን እናከብራለን።

**9.6 ከብዛት ይልቅ ለደህንነት እና ለጥራት ቅድሚያ መስጠት**: የተወሰነ ቁጥር ያላቸው ቃለ መጠይቆችን ለማድረግ በሚደረግ ግፊት ላይ በመመስረት ጥራትን፣ ጥበቃን ወይም ደህንነትን ጉዳት ላይ አንጥልም።

**9.7 የዘገዩ እና ከፊል መግለጫዎችን መረዳት**: የተጎጂው መረጃን የማካፈል ችሎታው እና ውሳኔው በመተማመን፣ በጊዜ እና በማገገም የሚታገዝ እና በጊዜ ሂደት እና በተለያዩ ግንኙነቶች ደረጃ በደረጃ ሊመጣ እንደሚችል እንገነዘባለን። በሚሰጡት ቃል መካከል መዛባት መኖር በተፈጥሮው ከስሜት መቃወስ፣ ከማስታወስ አቅም፣ ከመገለል፣ ከፍርሃት፣ ከጫና፣ ከባህል፣ ከተጠየቁት ጥያቄዎች፣ ከትርጓሜ እና የአድማጭ ስለተባለው ነገር ካለው እይታ ሊነሳ እንደሚችል እንገነዘባለን። በተፈጥሮ ከሚመነጩ  መሰል መዛባቶች ላይ ተመስርተን ስለ እውነተኛነት ግምቶችን አንወስድም።

## መርህ 10. በአክብሮት የተሞሉ እና ጥሩ ግንኙነቶችን መፍጠር

**10.1 *መገምገም እና ንቁ መሆን***: በግንኙነት መጀመሪያ ላይ፣ የደህንነት ስጋቶችን፣ የግል ህይወትን፣ የተጎጂዎች ፍላጎቶችን እና ደህንነታቸውን፣ በግንኙነታችን ውስጥ ያሉ ማናቸውንም ክፍተቶች እና በተጎጂ ላይ ለመቀጠል የሚደረጉ ማናቸውንም  ጫናዎችን እንደገና እንገመግማለን። እነዚህን ጉዳዮች በሙሉ እንከታተላለን። የምንቀጥለው ሙሉ በሙሉ ተጎጂን ስንረዳ እና ተጎጂ ሙሉ በሙሉ ሊረዳን ሲችል ብቻ ነው። ይህን የምንጠቀመው ማንኛውም አስተርጓሚ በተጎጂው ቋንቋ እና በእኛ ቋንቋ ለመስራት ችሎታ እንዳለው ማረጋገጥን ይጨምራል።

**10.2 የስሜት መቃወስን የሚረዱ ይሁኑ**: የስሜት መቃወስ እና የጭንቀት ምልክቶችን ለይተን ለማወቅ እና ለመከታተል፣ እንዲሁም  መስተጋብሩ ሊያስከትል የሚችለውን አስጨናቂ ውጤቶች መቼ እና እንዴት መቀነስ እና ምላሽ መስጠት እንደምንችል እናውቃለን። የስሜት መቃወስ  ክስተቶች በሚታወሱበት እና በሚቀርቡበት  ቅደም ተከተል እና ፍጥነት ላይ ተጽዕኖ እንደሚያሳድር እንረዳለን።

**10.3 የግል ቦታን ማክበር**: የተጎጂው አካላዊ ቦታ ላይ በግዴታእንዳንገባ እንጠነቀቃለን።

**10.4 ደህንነቱ የተጠበቀ የቃለ መጠይቅ ሂደት ይፍጠሩ**: ቃለ መጠይቁ ደህንነቱ የተጠበቀ እና ግንዛቤ ያለው ሂደት እና መዋቅር እንዳለው እናረጋግጣለን። ሰፋ ባለው የቃለ መጠይቅ ሂደት ውስጥ ማንኛቸውም የስልታዊ እና ከግጭት ጋር የተያያዙ የወሲባዊ ጥቃት ጥያቄዎች ደህንነቱ በተጠበቀ መልኩ መጠየቃቸውን እናረጋግጣለን። በአስተማማኝ እና ጥንቃቄ በተሞላበት መንገድ ቃለ መጠይቁን ለመዝጋት ጊዜ እንወስዳለን፣ እንዲሁም ለተጎጂዎች ያላቸውን ልምዳቸውን ለመናገር ለሰጡት ጊዜ እና ስለጥንካሬያቸው እናመሰግናለን። ከቃለ መጠይቁ በኋላ ምን መጠበቅ እንደሚችሉ፣ ስለሚያገኙት ድጋፍ እና ስለቀጣይ መረጃ ከተጎጂዎች ጋር እንነጋገራለን።

**10.5 ተጎጂዎች ታሪካቸውን እንዴት እንደሚናገሩ ቁጥጥሩን መስጠት**: ተጎጂዎች ልምዳቸውን የሚያካፍሉበትን መንገድ የመቆጣጠርን አስፈላጊነትን እናከብራለን። ተጎጂዎች ስለተፈጠረው ነገር በራሳቸው መንገድ፣ በራሳቸው ፍጥነት እንዲያብራሩ ቦታ እንሰጣለን  በንቃት እናዳምጣለን። የጥያቄዎቻችንን ፍጥነት እና ድምጸት እናስተካክላለን። ለጉዳት እና ለድጋሚ የስሜት መቃወስ ከፍተኛ ስጋት ስለሚፈጥር እና የተሰበሰበው መረጃ አስተማማኝ ያልሆነ ወይም የተሳሳተ ሊሆን ስለሚችል ተጎጂዎችን አናቻኩልም።

**10.6 ክፍት ጥያቄዎችን ይጠይቁ**: እኛ (እንደ ቃለ መጠይቅ አድራጊዎች እና አስተርጓሚዎች) ክፍት የሆኑ ጥያቄዎችን እንጠይቃለን። ዝግ የሆኑ ጥያቄዎች በተጎጂው ላይ እና በዚያ መንገድ በተሰበሰበው መረጃ ትክክለኛነት እና ዝርዝር ላይ ሊያስከትል የሚችለውን ጎጂ ውጤት እንገነዘባለን። እንደነዚህ ያሉ ጥያቄዎችን የምንጠቀመው በልዩ ሁኔታዎች ውስጥ ብቻ ነው።

**10.7 ስልታዊ እና ከግጭት ጋር የተያያዘ ወሲባዊ ጥቃትን በአውድ ውስጥ ማስቀመጥ :** ስልታዊ እና ከግጭት ጋር የተያያዘ ወሲባዊ ጥቃት ከሌሎች ጥሰቶች እና ጉዳቶች ተነጥሎ እንደማይከሰት እንገነዘባለን። ተጎጂዎች ሌሎች ያጋጠሟቸውን ወይም ያዩዋቸውን ጥሰቶች ወይም ጉዳቶች ለማሳወቅ ከመረጡ በትኩረት እና በአክብሮት እንቀበላለን።

**10.8 የማያስፈልግዎ ከሆነ አይጠይቁ**: ግልጽ፣ ሚስጥራዊነት ያለው ወይም የጾታዊ ጥቃት ምስላዊ ዝርዝሮችን በተመለከተ በተለየ ለዓላማችን በማያስፈልግበት ጊዜ ጥያቄ አንጠይቅም ወይም አንመረምርም። እንደዚህ አይነት መረጃ ከፈለግን ለምንድ እንደሆነ ለተጎጂ በማብራራት መልስ የመስጠት ወይም ያለመመለስ ውሳኔያቸውን እናከብራለን። እንዲሁም የተጎጂን ያጋጠመ ጉዳይን  ስናቀርብ ወይም ስንዘግብ እንደዚህ አይነት ዝርዝሮችን ዋና አናደርግም ወይም በስሜት በተሞላ መንገድ አይሆንም።

[1] ***ስልታዊ እና ከግጭት ጋር የተያያዘ የወሲብ ጥቃት (SCRSV)***: ሰፊ ትርጓሜ ነው። ስልታዊ እና ከግጭት ጋር የተያያዘ የወሲብ ጥቃት አስገድዶ መድፈርን፣ የወሲብ ባርነትን፣ የግዳጅ ዝሙት አዳሪነትን፣ የግዳጅ እርግዝናን፣ የግዳጅ ፅንስ ማስወረድን፣ በግዳጅ ማምከንን፣ የግዳጅ ጋብቻን፣ ለጾታዊ ጥቃት እና/ወይም ለብዝበዛ ዓላማ ሰዎችን ማዘዋወር እና ማናቸውንም ሌላ ዓይነት ተነጻጻሪ ክብደት ያለው በማንኛውም ሰው ላይ የሚፈጸም በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ከትጥቅ ግጭት ጋር የተያያዘ ወሲባዊ ጥቃትን ያጠቃልላል። እንዲሁም በሰላማዊ ጊዜ ወይም በሽግግር ወቅት ስልታዊ፣ አፋኝ፣ የተዋቀረ ወይም የፖለቲካ ጥቃት አካል የሆኑ ሲሆኑ እና መሰል ጥቃቶች ማህበረሰቦችን ለማሸበር ወይም ለማጥፋት ጥቅም ላይ የሚውሉ ድርጊቶችን ያጠቃልላል። ስልታዊ እና ከግጭት ጋር የተያያዘ የወሲብ ጥቃት እስከ ዓለም አቀፍ የዘር ማጥፋት ወንጀል፣ በሰብአዊነት ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች ወይም የጦር ወንጀሎች ሊደርስ የሚችል ነገር ግን በእነዚህ ብቻ ያልተገደበ ነው።

[2] ***"ተጎጂዎች" እና/ወይም"ተጠቂዎች"*: (የደንቡ የእንግሊዘኛ ቅጂ ሰርቫይቨር (Survivor) የሚለወን ቃል የሚጠቀም ሲሆን ይህ ቃል በ አማርኛ ቋንቋ አቻ ያልተገኘለት በመሆኑ በዚህ ሰነድ ላይ ተጎጂ የሚለውን ቃል መጠቀም አስገዳጅ ሆኗል። በመሆኑም በዚህ ሰነድ ውስጥ ተጎጂ የሚለው ቃል ሰርቫይቨር (Survivor) የሚለውን ቃል በመተካት ጥቅም ላይ የዋለ መሆኑን ከግምት ማስገባት ያስፈልጋል)** ደንቡ "ተጎጂ (ሰርቫይቨር)"ን ይጠቀማል ምክንያቱም ብዙውን ጊዜ እንደ አነቃቂ ስለሚቆጠር። "ተጠቂ" እና "ተጎጂዎች" የሚሉት ቃላት በተለያዩ መቼቶች እና ቋንቋዎች የተለያየ ትርጉም ሊኖራቸው ይችላል፣ እናም ጥቃት ያጋጠማቸው ሰዎች አንዱን ቃል ከሌላው ሊመርጡ፣ ወይም ሁለቱንም ላይመርጡ ይችላሉ። የተጎጂዎች የማንነት ምርጫዎች በአካባቢያቸው ባሉ ሰዎች ሊከበሩ እና ሊንጸባረቁ ይገባል። እንዲሁም አንዳንድ ተጠቂዎች ከጥቃት እንደማይተርፉ መቀበል አስፈላጊ ነው። ሕጉ ከተጎጂዎች ጋር በመሥራት ላይ የሚያተኩር ቢሆንም፣ የሕጉ ገጽታዎች በሕይወት ያልተረፉ የተጎጂዎችን የግል ሕይወት መብት እና መብቶች ለመጠበቅ ይሠራሉ።

[3] እ.ኤ.አ. በ 1989 በተባበሩት መንግስታት ድርጅት የህፃናት መብቶች ስምምነት ላይ እንደተተረጎመው።

[4] **ሥርዓተ-ጾታ**: በዚህ ደንብ ውስጥ 'ሥርዓተ-ጾታ' የሚያመለክተው በሮም ዓለም አቀፍ የወንጀለኞች ፍርድ ቤት ህግ አንቀጽ 7(3) ሥር ያለውን ፍቺ ነው፤ በህብረተሰቡ አውድ ውስጥ ሁለቱ ጾታዎች፣ ወንድ እና ሴት። ይህ ፍቺ የጾታ ማህበራዊ ግንባታን እና ተጓዳኝ ሚናዎችን፣ ምግባሮችን፣ ተግባራትን እና ባህሪያትን ለሴቶች እና ለወንዶች እና ለሴቶች እና ለወንዶች ልጆች

የተሰጡ መገለጫዎችን እውቅና ይሰጣል። ጎጂ የሥርዓተ-ፆታ ትርክቶች ሴቶችን እና ሴት ህፃናትን ተመጣጣኝ ባልሆነ መልኩ ይጎዳሉ። ሆኖም፣ ጎጂ የሥርዓተ-ፆታ ትርክቶች ለምሳሌ፣ ሁለትዮሽ ያልሆኑ ወይም ጾታን የማይከተሉ ሰዎችን፣ የተለያዩ ወሲባዊ ፍላጎት ያላቸውን ሰዎች፣ የሥርዓተ-ፆታ ማንነቶችን፣ የሥርዓተ-ፆታ መግለጫዎችን፣ የጾታ ባህሪያትን፣ እና ወንዶች እና ወንዶች ልጆችን ጭምር ይጎዳሉ።[5] **LGBTQI+** ምህጻረ ቃል (ሌዝቢያን፣ ጌይ፣ ባይ ሴክሹዋል፣ ትራንስጀንደር፣ ክዌር እና/ወይም እየጠየቀ ያለ/ያለች፣ ኢንተርሴክስ እና ሌሎች መደበኛ ያልሆነ የፆታ ማንነት ወይም ወሲባዊ ፍላጎት ያላቸውን ሰዎች) የተለያዩ ግለሰቦችን ያካተተ ቢሆንም፣ ሁሉን ያጠቃለለ፣ ወይም ሁለንተናዊ መደበኛ ምህጻረ ቃል አይደለም።

[6] ሰዎች ውስብስብ፣ ተለዋዋጭ የሆኑ እና ብዙ፣ ተደራራቢ እና ተለዋዋጭ ባህሪያት፣ መለያዎች ወይም ማንነቶች ያላቸው ናቸው። ብዙ ጊዜ ከአንድ በላይ መድልዎ ያጋጥማቸዋል፣ እንደ ግጭት፣ መፈናቀል፣ ድህነት፣ ወረርሽኞች እና በሽታዎች ባሉ ሁኔታዊ ሁኔታዎች ተጠቂ ናቸው ፣ በዚህም ምክንያት ወይም በሌላ መንገድ ደህንነትን፣ ጤናን፣ የህግ እና ሌሎች አደጋዎችን ይጋፈጣሉ። እነዚህን ሁኔታዎች መረዳታችን የተጎጂዎችን፣ ያጋጠሟቸውን ጥሰቶች፣ የሚያጋጥሟቸውን አደጋዎች፣ ተግዳሮቶች እና መሰናክሎች፣ መብቶቻቸውን እና ምኞቶቻቸውን እና የድጋፍ ፍላጎቶቻቸውን በተሻለ ለመረዳት እና እቅዶቻችንን እና አካሄዶቻችንን በትክክል እንድናስተካክል ይረዳናል ። ተጎጂዎች ሊያጋጥሟቸው የሚችሏቸው እንደዚህ ያሉ ***ባህሪያት፣ መገለጫዎች እና ማንነቶች*** እና ተዛማጅ ***የመድልዎ ዓይነቶች*** የሚከተሉትን ያካትታሉ: ዕድሜ (የብስለት ደረጃን ፣ የመሻሻል ችሎታዎችን ጨምሮ)፤ ጾታ እና ሥርዓተ-ጾታ (የሥርዓተ-ፆታ ማንነትን እና አገላለጾችን (ትራንስጀንደርን ጨምሮ፣ ሁለትዮሽ ያልሆኑ እና ጾታ ያለዩ) ጾታዊ ዝንባሌ የጾታ ባህሪያት (ኢንተርሴክስን ጨምሮ))፤ ዘር፤ ሃይማኖት፤ ብሔራዊ መነሻ፣፤ ማህበራዊ አመጣጥ፤ ጎሳ (የአገሬው ተወላጅ ቡድኖች፣ ባህል እና ወጎች ጨምሮ)፤ አካል ጉዳተኝነት፤ የቤተሰብ ሁኔታ ወይም ደረጃ፤ የትውልድ ሁኔታ፤ ማህበራዊ-ኢኮኖሚያዊ ክፍል፣ መደብ ወይም ደረጃ፤ የጤና ሁኔታ ወይም ደረጃ፤ ዜግነት፤ እንደ ስደተኛ፣ ፍልሰተኛ ወይም ሌላ ያለ የመኖሪያ ሁኔታ፤ ትምህርት እና ማንበብና መጻፍ፤ ህጋዊ ሁኔታ፤ እና የፖለቲካ እምነቶች፣ አስተያየቶች ወይም ግንኙነት። ይህ አጠቃላይ ዝርዝር አይደለም። ተጎጂዎች አብዛኛውን ጊዜ፣ ብዙ አይነት የተቀላቀሉ የመድልዎ ዓይነቶች ያጋጥማቸዋል። ብዙ አይነት አድልዎ እና እኩልነት አለመኖር ሲደራረቡ፣ “የመገናኛ ምክንያቶች” ይባላሉ።

[7] ***ምክንያታዊ ማሻሻዮች*** ማለት “ያልተመጣጠነ ወይም ተገቢ ያልሆነ ሸክም የማያሳድር አስፈላጊ እና ተገቢ ማሻሻያ እንዲሁም ማስተካከያ፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ለአካል ጉዳተኞች ከሁሉም ሰብአዊ መብቶች እና መሰረታዊ ነጻነቶች በእኩልነት መጠቀማቸውን ለማረጋገጥ" (አንቀጽ 2). የአካል ጉዳተኞች መብቶች ስምምነት 2014)

[8] ***አራት መሪ መርሆች*** በተባበሩት መንግስታት የህጻናት መብቶች ስምምነት ላይ እንደተቀመጠው:

- **አድሎ አለመደረግ** (አንቀጽ 2) ፡- “በሥራችን ወቅት ህፃናትን ለየትኛውም ዓይነት መድልዎ አለመዳረጋችንን እናረጋግጣለን። የህፃናቱ ወላጆች ወይም ህጋዊ አሳዳጊዎች፣ ዘር፣ ቀለም፣ ጾታ፣ ቋንቋ፣ ሃይማኖት፣ የፖለቲካ ወይም ሌላ አመለካከት፣ ብሔር፣ ጎሳ ወይም ማህበራዊ ዳራ ድህነት፣ የአካል ጉዳት፣ የትውልድ ወይም በሌላ ሁኔታ ምንም ይሁን ምን ከህፃናት ጋር አብረን እንሰራለን።
- **የህፃኑ የላቀ ጥቅም** (አንቀጽ 3)፡- “ልጆችን በሚነኩ ድርጊቶችና ውሳኔዎች ሁሉ የህፃኑ ጥቅም ቅድሚያ የሚሰጠው መሆኑን እናረጋግጣለን። የህፃኑን ጥቅም ከሌሎች ጉዳዮች ጋር ለማመጣጠን ባለ ሁለት ደረጃ አቀራረብ ያስፈልጋል
- ***የመኖርእና የማደግ መብት*** (አንቀጽ 6)፡- “ከልጆች ጋር ያለን ግንኙነት የልጁን በላቀ መንገድ የማደግ መብት ማለትም በአካል፣ በአእምሮ፣ በመንፈሳዊ፣ በሥነ ምግባራዊ እና በማህበራዊ ጉዳዮች ላይ እንቅፋት እንደማይፈጥር እናረጋግጣለን። ተገቢውን ምላሽ እና ድጋፍ በመስጠት ጭምር በልጁ ህይወት፣ ህልውና እና እድገት ላይ የሚደርሰውን ማንኛውንም አደጋ ለመቀነስ ተገቢውን የአደጋ ግምገማ እና ሁሉንም ጥረቶች እናደርጋለን።

**የአንድ ሰው ሃሳቡን የመግለጽ እና ከግምት ውስጥ እንዲገባ የማድረግ መብት** (አንቀጽ 12)፡- “አንድ የራሱን ወይም የራሷን አመለካከት መመስረት የሚችል/የምትችል ልጅ እራሱን ወይም እሷን በሚመለከቱ ጉዳዮች በነፃነት ሀሳብን የመግለፅ መብት እንዳለው/እንዳላት) እንገነዘባለን። ሂደቱን በተቻለ መጠን አሳታፊ ለማድረግ እና የልጁን/የልጅቷን አመለካከት በእድሜ/እድሜዋ እና በብስለቱ/ብስለቷ መሰረት ተገቢውን ክብደት ለመስጠት እንሞክራለን። እንዲሁም የአንድን ህፃን የመሳተፍ መብት መረጃን እና ምክሮችን ህፃኑን ባገባዘበ መልኩ የመቀበል እና እያደገ የሚመጣ አቅሙን/አቅሟን የሚያገናዝብ መብት መሆኑን እንረዳለን።